# አዎን ዛሬ ሁላችንም እስክንድር፣ ሁላችንም አንዱዓለም ነን፣ **ነገስ**?

**"በፈርስ የሚያጓጉር ከብት ብቻ ነው!" እና እስኪ መርዶ መቀበልን በቃ እንበል!**

*የግል አስተያየት፦ አያል ሰው ደሴ - መስከረም ሁለት-ሽህ-አራት ዓ/ም*

ሰሞኑን የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በአገራችን ያለውን አስከፊና አስጊ ሁኔታ በመቃዎም እና የሕዝባችንን እሮሮ እንደሌለ መቁጠርም ሆነ በዝምታ ለመመልከት ኅሊናቸው ያልፈቀደላቸው እንደ አቶ አንዱዓለም አንዳርጌና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን የመሰሉ ዜጎችን በተለመደ እብሪት ወደ-እስር እንደወረወራቸው ይታወቃል። ለዚኽ የግፍ እርምጃ ሰለባ የሆኑት ወገኖች ግን በተለይ ከዥዎቹ ድርጅታዊ ባኅሪና የቆየ ታሪክ አኳያ የተያያዙት ሰላማዊ ትግል ይኽን ሊያስከትል እንደሚችልም ሆነ ይኽንን ዋጋ እንደሚጠይቅ ዘንግተውት አይደለም ድምፃቸውን ማሰማትና የኅሊናቸው ተገዥ መሆንን የመረጡት።

ኢትዮጵያውያን፣ በተለይም ከአገር-ውጭ የሚገኙና ድንፃቸውን በነፃነት ማሰማት የሚችሉ ወገኖች፣ በእነዚኽ ዜጎች ላይ የተፈጸመውን ግፈኛና አፋኝ ድርጊት እየተቃወሙ፣ እያወገዙና የታሰሩት የኅሊና እስረኞች በአስቸኳይና ያለ-ምንም ቅድመ-ሁኔታ እንዲፈቱ ***"ዛሬ እኔም እስክንድር ነኝ! ዛሬ እኔም አንዱዓለም ነኝ!"*** ብለው በመንቀሣቀስ ላይ ናቸው። አዎን፣ ማንኛውም ለፍትኅ፣ ለሕግ-የበላይነትና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆመ ሁሉ ይኽንን መፈክር አንግቦ መንቀሣቀስ ይገባዋል።

በመሠረቱ ግፍ የፍራቻ ውልድ ነው ማለት ይቻል ይመስለኛል። ግፈኞች ደግሞ በተፈጥሮአቸው ከመጠን ያለፈ እራስ-ወዳዶች፣ ተጠራጣሪዎችና ጥላቸውንም የማያምኑ፣ ፈሪዎችና አብዛኞቹ በበታችነት ስሜት የተጠቁ፣ እራሣቸውን ከማንምና ከምንም በላይ የሚያዩና የሚሠሩት ሁሉ ልክ ነው ብለው የሚያምኑ ግብዝ ፍጡሮች ናቸው። ባላቸው አይተማመኑም፤ የያዙት ከእጃቸው እንዳይወጣ፣ ያገኙትንም ላለመልቀቅ ሁሌ ይሰጋሉ። ጥይት እንደሳታት ሚዳቋ ሁል-ጊዜ ይበረግጋሉ። በጫንቃው ላይ የተቀመጡበትን ሕዝብ ጨርሶ አያምኑትም፤ በጣም ይፈሩታል። ከዚኽ ስጋታቸው በመነሣትም ማንኛውንም ቅሬታም ይሁን ተቃውሞ አቅራቢ በ"ጠላትነት" ይፈርጃሉ። "ጠላት" ብለው የሚፈርጁት ሰው እንደነሱ ነፃ መሆንን እንደሚፈልግ፣ ሰብዓዊ ፍላጎቶች እንዳሉት፣ የሚወዳቸውና የሚወዱት፣ የሚያስብላቸውና የሚያስብላቸው ልጅ፣ ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ ዘመድ እንዳለው ሣይሆን እንደ ስሜት-የለሽ ግዑዝ ነገር ይቆጥሩታል። ለእነሱ አንዴ "ጠላት" ብለው የመደቡት ሰው ሰው መሆኑ ቀርቶ እሱ ይወክለዋል የሚሉትን አስተሣሰብ፣ ጎሣ፣ ቋንቋ፣ እምነት፣ ወዘተ ሆኖ ቁጭ ይላል። እሱን በማሰቃዬትና በመጉዳት፣ ያ "ጠላት" ያሉት ሰው የቆመበትን ወይም ቆሞለታል የሚሉትን እምነት፣ ፍልሥፍናም ሆነ ዓላማ የሚጎዱት ይመስላቸዋል። እሱን በማጥፋት ከሱ ኋላ ያለውን እምነትና ዓላማ የሚያጠፉ ይመስላቸዋል። በሚወስዷቸው የግፍ እርማጃዎች አማካይነት የበላይነታቸውን ምን ጊዜም ማረጋገጥ የሚቻል ይመስላቸዋል። በሕዝብ ላይ በተለይ ተቀናቃኝ በሚሏቸውና በሚቃዎሟቸው ላይ እንደ-ምንም የበላይነታቸውን በማሣየት ይረካሉ። ለግፍ ፈጻሚው ግፍ የሚደስበት ሰው ሰብዓዊ ተፈጥሮው አይታየውም። ያን ሰው የሚያየው እንደራሱ ሰው አድርጎ ሣይሆን በጠላትነት የተፈረጀ ድርጅት፣ የጎሣ ይሁን የቋንቋ ወይም የሐይማኖት ቡድን ግርዶሽ ሆኖ የሚታይና ምንም ዓይነት ሰብዓዊ ፍላጎቶችና ስሜቶች ያሉት ሆኖ አይታይም።

ናዚዎች አይሁዶችንና "አነስተኛ ሰብዓዊ ፍጡር" የሚሏቸውን በመጨፍጨፍ፣ ዘረኞች እነሱን ያልመሰሉትን ሌሎች በመጨቆን፣ ዝቅ-አድርጎ በማየትና በማሰቃየት፣ ተፈጥሮአዊ መብቶቻቸውን በመንፈግ፣ ዘመናዊ ዴሞክራሲን መሠረትን ብለው የሚመፃደቁ አሜሪካውያን ጥቁሮችን የዜግነት መብት መንፈግ ብቻ ሣይሆን "ሦስት-አምስተኛ ሰው" በማለት "በእግዚአብሔር ሥር ያለችና የማትከፋፈል" አገር የሚል ምፀታቸውን ሲገልጡ፣ "እግዚኣብሔር ፍቅር ነው፣ ሁሉንም የሰው ዘር የፈጠረ እሱ ነው" የሚል ስብከታቸውንና የእምነታቸውን ጥናት በአፋቸው አንድ ጎን እየሰበኩ በሌላ በኩል እኔ እንደማምነው ያላመነን ለዚያው 'ሁሉን በአምሣያውና በእኩልነት ፈጥሯል፣ ሁሉንም እኩል ይወዳል' ለሚሉት እግዚኣብሔር ሲባልና በሱም ስም መግደል ለፅድቅ ያበቃል ሲሉ፣ ወዘተ.. የሰውን ልጅ ሕይዎት ክቡርነትና ሁሉም እንደ-እነሱ የተሻለ ሕይዎትን ፈላጊ፣ በነፃ ኣእምሮው የፈለገውን የማሰብና የመወሰን ችሎታም መብትም እንዳለው ካለመረዳት ነው። ታዲያ ናዚዎች በአይሁዶች ላይ በአይሁድነታቸው ብቻ ያንን ሁሉ አሰቃቂ ግፍ ሲፈጽሙ ሌላው በዝምታ በማየቱ እንግሊዞችም፣ ፈረንሣዮችም፣ ቼኮችም፣ ፖሊሾችም፣ ራሻዎችም፣ ወዘተ.. ከነዚኽ በሰው ልጅ እኩልነት ከማያምኑ አረመኔዎች የጭካኔ ዱላ አላመለጡም። በአይሁዶች ላይ የደረሰውን ግፍ

“አይሁድ” ከሚለው መጋረጃ ኋላ ያሉትን ሰብዓዊ ፍጡሮች እንደ ማንኛውም የሰው ልጆች ሰው ከመሆናቸው አኳያ በጊዜው አለመታየቱ ሚሊዮኖች በግፍ እንዲያልቁ ሆነ።

በአገራችንም ለኢትዮጵያችን ክብር አኩሪ የጀግንነት ሥራ የሠሩ፣ በመስዋዕትነታቸው አገራቸውንና ሕዝባቸውን ያስከበሩ ዜጎች ላይ ግፍ ሲፈጸምባቸው፣ እንደ ዶሮ አንገታቸው ተቀልምሞ ሲገደሉ፣ “ኢሕአፓ ናችሁ፣ ኢድኅ/ዩ ናችሁ”፣ ወዘተ ተብለው በጅምላ ሲጨፈጨፉ፣ አይ የለም ፍትኅ ተጓደለ፣ ሰብኣዊ ክብር ተጣሰ፣ ሕግ ጠፋ ተብሎ፣ ግፍ የተፈፀመባቸውን ዜጎች አባል ናቸው ከተባሉባቸው ድርጅቶች በላይ በቅድሚያ እንደ ሰብዓዊ ፍጡርና ከዚያም እንደ-ኢትዮጵያዊ ወገን ስላልታዩ ሁሉም የየራሱን አዘን፣ ንዴትና ቂምን ያዘለ ቁጭት ተሸክሞ መቀጠልን ነው የመረጠው። በየጊዜው የሚተኩ ግፈኞችም በዜጎች ላይ የየራሣቸውን ግፍ ከመቀጠል፣ ኅብረተሰባችን በአጠቃላይ ፍትኅ መነፈጉንና ሰብኣዊ ክብሩን ማጣቱን ማስቆም አልተቻለም። በየጊዜው ታዋቂ ሰዎች ሲታሰሩ ወይም ሲገደሉ ብቻ ምን-ጊዜም ያልቆመው የሰብዓዊ መብት ረገጣውና በዜጎች ላይ የሚደርሰው ግፍ ጎላ ብሎ ይታይና ሁሉም በተለይም ለውጥ እንዲመጣ የሚታገለው ክፍል፣ ግፍ የሚፈጸምባቸው ዜጎች የቅርብ ቤተሰቦችና የየድርጅቱ አባሎች መንቀሣቀስ ይጀምራሉ። ይኸን በየጊዜው የሚከሰት ሁኔታ ከሥር-መሠረቱ ለማስቀረት የሚያስችል እንቅስቃሴ እንደ-ኅብረተሰብ ባለ-ማድረጋችን መርዶ መቀበልን በቃ ማለት አልቻልንም። ይኸ ብቅ-ጥልቅ የሚል እንቅስቃሴ በአገራችን ፍትኅን በቋሚነት እንዲሰፍን የሚያደርግ ስለማይሆን ደግሞ ከሰውነት ደረጃ የሚያወርደንና “በፈርስ የሚያጓጉር ከብት ብቻ ነው” የሚለውን ብኂል የሚያስከትልብን ይሆናል። (*1)

ማንም ኅሊና ያለው ሰብዓዊ ፍጡር በማንኛውም ሰው ላይ የሚደርስን ኢ-ፍትኃዊና የግፍ እርምጃ መቃዎም ፖለቲካዊ ሣይሆን መሠረታዊ የሰብዓዊነት እርምጃ ሆኖ ሊወሰድም፣ ሊቆጠርም ይገባል። ይኸ ደግሞ በራሣቸው ግፍ በሚፈጽሙ ሰዎች ላይ ጭምር የሚወሰድንና የሚፈጸምን እርምጃ ሁሉ ይመለከታል። ፍትኅ ለማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር፣ በሌላው ላይ ግፍ ለሚፈጽሙ ጭምር፣ በእኩል የሚሠራ መሆን ይኖርበርታል። ለእነዚኸ ግፈኞች ሰብዓዊ መብት አለ-መቆም ከፍትኃዊነትም ሆነ ከሰብዓዊ አስተሣሰብ የመነጨ አይሆንም። ፍትኅን በዚያ መሠረታዊ የእኩልነት መንፈስ አለማየት ፖለቲካዊ የወገንተኝነት አቋም ይሆናል። በመሠረቱ ያ ዓይነት የሰውን ልጅ በእኩል ዓይን ያለ-መመልከት ጥንውት የፍትኅ መዛባትን ያስከትላል።

ማንም መንግሥት ሕግ ማስከበር እንደሚጠበቅበት ግልጥ ነው። መቸም ጥፋት ያጠፋ በሕግ አይጠየቅ የሚል አይኖርም። ሕጋዊ እርምጃ ከበቀል እርምጃ የሚለየው በሕግ ፊት ከሣሽም ተከሣሽም በእኩል ዓይን መታየታቸው ብቻ ሣይሆን ክሱ ሕጋዊ ሂደቱን በአግባቡ ሲጨርስ የሚወሰደው የቅጣት እርምጃ ተሠራ የተባለውን ወንጀል/በደል የሚመጥንና ተበደልኩ ላለው ክፍል ተመጣጣኝ ፍትኅን የሚሰጥ እንጂ ቂም መወጫ አድራጎት አለ-መሆኑ ይመስለኛል። ለዚኸም ነው “ፍትኅ ዓይን የለውም” የሚባለው። ያ አባባል በፍትኅ ዓይን ማንም ሰው ቀለሙ፣ ዘሩ፣ ፆታው፣ የኑሮ ደረጃው፣ የፖለቲካ አቋሙም ሆነ መንፈሣዊ እምነቱ  ጨርሶ ግርዶሽ ሊሆንና በሂደቱም ሆነ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ጫና ሊያሣድርና ሊያጠላ እንደማይገባ የሚገልጥ ነው።

መንግሥታዊ ሥልጣን በያዘም ይሁን በማንም አካል/ተቋምና ግለሰብ በኩል በተከሣሽ ላይ ክስ ከመመሥረት ጀምሮ እስከ ተመጣጣኝ የቅጣት እርምጃ መውሰድና ማስወሰድ አዲስ አይሆንም። ጥያቄው ያለው ግን ሚዛናዊና ፍትኃዊቋ የመሆኑ ላይ ነው። ማንኛውም የሚወሰድ 'ሕጋዊ' እርምጃ ተቀባይነት የሚኖረው የሕግ የበላይነት በሰፈነበትና እራሱ መንግሥትና ሥልጣን ላይ ያሉትም በሕግ ፊት እኩል በሚሆኑበትና ለሕግ ተገዥ መሆናቸው በተግባር ሲገለጥ ብቻ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ገዥዎች እነሱን በእነሱነታቸው ሣይሆን በአገርና በዜጎች ላይ የሚፈጽሟቸው ዝም ተብለው ሊታለፉ የማይችሉ፣ ሕገ-ወጥና መረን-የለቀቁ የግፍ ድርጊቶቻቸው ትክክል አለመሆናቸውን በሚጠቁሙ፣ አድሎዓዊነትና ሙስና እንዲወገድ፣ እኩልነት እንዲረጋገጥና ፍትኅ እንዲሰፍን በሰላማዊ መንገድና እራሣቸው ባወጡት ግን ጨርሶ በማያከብሩት ሕግ መሠረት በመናገራቸው ወይም በመጻፋቸው ምክንያት እንዳሻቸው ያስራሉ፣ ያንገላታሉ፣ የጭካኔ እርምጃም ይወስዳሉ።

እንደነ አቶ መለስ ዓይነቱ ሰው ደግሞ ዕድሜአቸውን ባሣለፉበት ድርጅት ውስጥ 'ቀድሜህ ልሙት' በሚሏቸው የትግል ወንድሞቻቸው ላይ ሣይቀር “በትግሉ ዓላማ” ስም ዘግናኝ እርምጃ መውሰድና መግደል ምንም አዲስ ነገር ተደርጎ የማይወሰድ፣ በወሰዷቸውም የግፍ እርምጃዎች አንድም ጊዜ አንዳች ተጠያቀቂነት ደርሶባቸው የማያውቅና እራሣቸውን ከሕግ በላይ ሲያዩ የኖሩ በመሆናቸው “በአገር ደኅንነት” እና “ፀጥታ” ስም እንደ መርፌ ራስ በጠበበች መሠረት ላይ የቆመ ሥልጣናቸውን እንደ-ምንም ለማቆየት ንፁኃን ዜጎችን በሰበብ-አስባቡ ማሰር፣ ማንገላታትና ማሰቃየታቸው አዲስ ክስተት ሆኖ ሊወሰድ አይችልም። ለእንደነዚኸ ዓይነት በአምባ-ገነንነት

ተኮትኩተው ያደጉ ሰዎች አዲስ የሚሆንባቸው የምትሠሩት ልክ አይደለም፣ ተጠያቂ ሁኑ፣ ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ሲቀርብባቸው ነው፡፡

ስለ-ሆነም ነው በበኩሌ አዲስ የሚሆንብኝ የእነሱን እርምጃ እንደ-አዲስ ጉድ የሚመለከቱ ወገኖች ምላሽ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአቶ መለስ አገዛዝ በነ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እና እንደ አቶ ዓንዱዓለም አንዳርጌ የመሰሉ በኢሕአዴግ "ሕግ" ተመዝግበው ሰላማዊ ትግል በሚያደርጉ ድርጅቶች የአመራር አባላት ላይ በቅርቡ የተወሰደውንና እየተወሰደ ያለውን እርምጃ ቁጥራቸው ከቀን-ወደ-ቀን እየጨመረ የሄደ ኢትዮጵያውያን "ዛሬ እኔም እስክንድር ነኝ፣ አንሱዓለም ነኝ..፣" እያሉ ድምፃቸው ለታፈነ ሁሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማሰማት ላይ ይገኛሉ፡፡

አዎን ትላንት "ዛሬ እኔም ብርቱካን ነኝ! ኃይሉ ሻውል ነኝ! ታዬ ወልደ ሰማያት ነኝ! መሥፍን ወልደ-ማርያም ነኝ!..." ብለን እንደተንቀሣቀስን ሁሉ **"ዛሬ ሁላችንም እስክንድር፣ አንዱዓለም፣ ወዘተ ነን!"** ማለት ይኖርብናል፡፡ ሆኖም ያ በየጊዜው የሚደረግ መፈክር-አንጋቢ እንቅስቃሴ የነ አቶ መለስን ቀጣይ የግፍ እርምጃ ማስቆም እንዳላስቻለ ግልጥ ነው፡፡ ያም የሆነው እንቅስቃሴኣችን የሚያፈስ ጣራውን እንደምንም አንዴ ከመድፈን ይልቅ ክረምት ክረምት ሲመጣ ወይም የዝናም ወራትን እየጠበቀ ከጣራው የሚንጠባጠበውን በካይ ፍሣሽ በማቋቻ ዕቃ መቀበልን የመረጠውን ሰነፍ ሰው ስለሚመስል ነው፡፡ የግፉ ምንጭ ካልደረቀ ነገም በሌሎች እስክንድሮች፣ በሌሎች አንዱዓለሞች ላይ መድረሱ እንደሚቀጥል ሊታወቅ ይገባል፡፡

በአገራችን ፍርደ-ገምድል ብይኖች የወለዷቸው ግፎችና ሰቆቃዎች እንዲቆሙ ሁለት ነገሮችን በጥሞና ማገናዘቡ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

*አንደኛ፣* እንደ ኅብረተሰብ በፍትኅና በሕግ የበላይነት ላይ ያለንን መሠረታዊ ግንዛቤ ማስተካከል ይመስለኛል፡፡ ያም ማለት ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰው ፍትኅ ለማንኛውም የሰው ልጅ ሊነፈገው የማይገባና የማንኛውም ዜጋም ሆነ ማኅበረሰብ የሰላማዊ ኑሮው ዋና ዋቢና ጠበቃው እንዲሁም ሰብዓዊ መተማመኛውና ዋስትናው እንደሆነ በተገቢ መገንዘብ ነው፡፡ ያ ደግሞ ፍትኅ ከፖለቲካ አቋምም ሆነ ከመሣሰሉት ወገንተኝነትን የግድ በሚጠይቁ አመለካከቶችና የበቀል እርምጃ በአንድ በኩልና በሌላ በኩል በፍትኅ መኻል ያለውን ልዩነት ለይቶ ማወቅን ይጠይቃል፡፡ ይኸም በተራው የኅሊና ተገዥ የሚያደርግ መሠረታዊ የአስተሣሰብ ለውጥን ይጠይቃል፡፡

*ሁለተኛ፣* ይኸ ለማንም ሰብዓዊ ፍጡር ሊነፈግ የማይገባው ከባድ እሴት በሁሉም ዘንድ እንዲሰፍንና እንዲሰርፅ፣ ፍትኅ እንዲሁ በነፃ የማይገኝ መሆኑን መረዳትና በራስ ላይ የአስተሣሰብና የአመለካከት ለውጥ ከማድረግ ጀምሮ የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል፡፡ ይኸም ማለት ማንኛውም ግፍ በማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ላይ ሲደርስ ወይም ሲፈጸም በዝምታ አለማየትና ግፉ እንዲቆም፣ በግፍ ፈጻሚው ላይ አስፈላጊው ሕጋዊ ተጠያቂነት እንዲኖር፣ ለተጠቂው ፍትኅና የሚገባ ካሣ እንዲያገኝ ጠንክሮ መቆምንና ለዚኸም ቦግ-እልም የሚል ሣይሆን ያልተቋረጠ ዓለም-አቀፍ ይዘት ያለው አገር-አቀፍ ትግል ማድረግን ይጠይቃል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቶቹን የተሻለ የሚያከብርበት፣ ሰብዓዊ ክብሩ የሚጠበቅበት፣ እኩልነት የሚረጋገጥበትና ኑሮው የሚሻሻልበት ሥርዓት በመሻት በአፄ ኃይለ-ሥላሴ ዘውዳዊና ባህላዊ መንግሥት ላይ ሲነሣ ኅሊና-ቢሶቹና ትንሽ አሳቢዎቹ የደርግ ጥርቅሞች በድንቁርና መንፈስ አፄ ኃይለ-ሥላሴን እና ተከብረው አገራቸውን በዓለም ፊት ሣይቀር ያስከበሩ ዜጎችን ያለ-ምንም ሕጋዊ ሥርዓት በግፍ ሲረሽኑ አብዛኛው ድንዛዜ በተሞላው ዝምታ፣ በጣም ጥቂቶች ደግሞ የእነኝኸ ኢትዮጵያውያን በተገደሉበት ሁኔታ መገደል ለዘመናት የተጠራቀሙ ችግሮችን የሚያስወግድ ይመስል በ"እሰየው" መቀበልና እንደ-"አይቀሬ ክስተት" መቆጠሩ ይታወቃል፡፡ ከዚያ ቀደም-ሲል በታኅሣሡ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ እነ እራስ አበበ አረጋይን በመሰሉ ምርጥ አርበኞች ላይ እንደተወሰደው የደመ-ነፍስ እርምጃ ሁሉ በደርግ ያልበሰሉ ግብዞችም እንዲሁ አገራቸውን ከአበኝነት ጀምሮና በልዩ ልዩ መስክ ያገለገሉ ዜጎች ላይ የተወሰደ እርምጃ በአገራችን የተፈጸመ የመጨረሻ ሕገ-ወጥ የግፍ ድርጊት ሊሆን አልቻለም፡፡ ያ የግፍ እርምጃ እንዳይቀጥል ማድረግ ይቻል የነበረው ግን ጉዳዩን የግድ ግፍ ከተፈፀማቸው ግለሰብ ኢትዮጵያውያን፣ ከነበራቸው ሥልጣንም ይሁን ለአገራቸው ካበረከቱት አኳያ በማየት ብቻ መሆን አልነበረበትም፡፡ እነዚኸ ዜጎች ከምንም በላይ ሰብዓዊ ፍጡራን መሆናቸው ቀድሞና ጎልቶ ሊታይ በተገባ ነበር፡፡ በሕግ ፊት ቀርበው መብቶቻቸው ተከብረውላቸው በሞት የሚያስቀጣ ፍርድ እንኳን ቢወሰንባቸው ለማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር የሚገባው የመጨረሻ ክብር ሊነፈጋቸው ባልተገባ ነበር፡፡ አልፎም በዕድሜአቸው፣ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ባበረከቷቸው ሁሉ ተገቢው ክብር በተገባቸው ነበር፡፡ ያ የዝምታ ምላሽ፣ አገሪቱ ልታጣቸው የማይገባ ዜጎቿን ማጣት ብቻ ሣይሆን ባሕላዊ እሴቶቻችንንም ጭምር እንድናጣና ለጥራዝ-ነጠቅ አስተሣሰቦች ተገዥ ባልሆንም ነበር፡፡

ያ ባለመደረጉና እነዚያን ኢትዮጵያውያን ከሰብዓዊነት አውጥተን በማየታችን የግፍ አዙሪቱ መቀጠሉ፣ ተዋናዮቹ ቢቀየሩም የሕግ የበላይነት ትርጉም ማጣቱ ቀጠለ፡፡ ወላጆች በልጆቻቸው ሞት

እንዳያለቅሱ ብቻ ሣይሆን እንዲያውም እንዲዘፍኑ፣ የልጆቻቸውንም ሬሣ እንዲገዙ ተገደዱ:: በዚኽ መልክ ሬሣ በሚከበርበት አገራችን ላይ የሰው ልጅ (የዜጎች) ሕይዎት ምንም ዋጋ እንደሌለው ሆኖ እንዲታይ ተደረገ:: “ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል” እንዲሉ፣ ኃይል መጠቀምና ግድያን የችግሮች መፍቻና የልዩነቶች ማስተናገጃ አድርገው የሚቆጥሩ፣ በመርዘኛ ፖለቲካዊ-ጎሠኝነትና በዞረበት ግራ-ዘመም የፖለቲካ ፍልሥፍና የተነኩ፣ የኢትዮጵያን ታሪክና ባኅላዊ እሴቶቿን የሚንቁ ጥራዝ-ነጠቅና አጉራ-ዘለል የሕወሓት/ወያነ አመራር ቁንጮዎች ከደርግ ሥልጣን ሲቀሙ ከላይ ለውጭ ፍጆታ ያኽል ዴሞክራሲያዊ ሆኖ ለመታየት ቢሞክሩም ልብሣቸውን እንጂ ውስጣዊ እምነታቸውን መጣልና መቀየር አቅቷቸው የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች መርገጥና አገር-ገዳይ መርኃ-እቅዶችን (ፖሊሲዎችን) መከተል ሥራዬ-ብለው ተያያዙት::

በንፁኃን ደም የተቀደሰው ደርግ በከተሞች ውስጥ ወጣቱንና ምሑሩን እየጨፈጨፈ በአደባባይ ሬሣ ሲጥል፣ በባዕዳን እንኳን ያደርገዋል ተብሎ የማይታሰብ ሰቆቃና ግፍ በዜጎች ላይ ላደረሰው አሥራ-ሰባት ዓመት የዘለቀ ዘግናኝ አገዛዙ መንደርደሪያው እንዳደረገው ሁሉ፤ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አፍላ መሪዎች የኤርትራ ጉዳይ ሕዝብ በመከረበት ሕጋዊ መንገድ እንዲታይ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ያቀረቡ ተማሪዎችን በአደባባይ በመጨፍጨፍ የግፍ አገዛዛቸውን ሲጀምሩ አገራችንና ሕዝባችን ለዘላቂ ሰቆቃ እየተመቻቹ መሆናቸው ግልጥ በሆነ ነበር::

እነ ክቡር ፕሮፌሰር አሥራትን በሰበብ አስባቡ አስሮ በቂም-በቀልና በፍራቻ መንፈስ ሲያሰቃይ፣ አሰፋ ማሩን በጠራራ ፀሐይ ሲረሽን፣ “ዛሬ እኔም አሥራት ወልደየስ ነኝ፣ ዛሬ እኔም አሰፋ ማሩ ነኝ!” ብለን ፀንተን ባለመቆማችን ድርጊቱ መልኩን ሣይቀይር ስፋቱንና መጠኑን እየጨመረ ከመሄድ አላስቆምንም:: ግፍ ፈጻሚዎቹም በዕብሪታቸው እንዳይቀጥሉ አላደረግንም:: ቀደም-ሲልም እነዚያ በታኅሣሡ መፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ ሣቢያም ሆነ በኋላ በደርግ ደናቁርት የተወሰዱ አረመኔአዊ እርምጃዎች መታየት የነበረባቸው “በጠላቶች” ላይ የተወሰዱ አዘቦታዊና “አይቀሬ ሕጋዊ” እርምጃዎች ሆነው ሣይሆን በሰው ልጆች (በዜጎች) ላይ የተፈጸሙ ከፍተኛው የሰው ልጅ መብት ጥሰትና መሠረታዊ የፍትኅ መጓደል እንደሆኑ ነበር መታየት የነበረባቸው::

በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ሰው ላይ የሚፈጸም ሰብዓዊ መብትና ክብር ረገጣ (ጥሰት) ሁሉ በራሱ በፍትኅ ላይ የተወሰደ እርምጃ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል:: እነ-አቶ መለስ ዜናዊ በድርጅታቸው ውስጥ የትግል ጓዶቻቸው ላይ በወሰዷቸው እርምጃዎች፣ እነ ፀጋዬ ገብረ-መርድኅንን የት እንዳደረሷቸው የተጠያቂነት ዋጋ ባለ-መክፈላቸው በድርጅታቸው ከፍተኛ አመራር አባላት በነ አቶ ሥዬ አብርሃ፣ ተሸክመው ተከዜን ባሻገሯቸው አጃቢዎቻቸው እነ አቶ ታምራት ላይኔ ላይ የመሰላቸውን ብይን ቢሰጡ ተጠያቂነት እንደማይገጥማቸው አውቀዋል:: እነ ታምራት፣ እነ ሥዬ ሲታሰሩ “ያው እርስ-በርስ ነው፣ የእጃቸውን ነው፣ ወዘተ..” በማለት ፋንታ ከታምራትና ከሥዬ ኋላ የተጣሰውና የተረገጠው ፍትኅ እንደሆነ በመገንዘብ ለፍትኅና ለሕግ የበላይነት ቀጣይ ትግል ባለ-መደረጉ፣ እነ አቶ መለስ በተጠያቂነት-አልባ እርምጃዎች እንዲቀጥሉ፣ የጥፋት ሠይፋቸው በሌሎች ንፁኃን ዜጎች ላይ በቀጣይነት እንዲያርፍ ሁኔታዎችን አመቻችቷል::

ስለ-ሆነም ይኽ የመከራ፣ የሰቆቃ፣ የሰብዓዊ መብትና ክብር ጥሰትና የፍትኅ መጓደል ሂደት እንዲያከትም “**ዛሬ እኔም እስክንድር ነኝ!” የሚለው እንቅስቃሴ ዓለም-አቀፍ ይዘት እንዲኖረውና ነገም፣ ተነገ-ወዲያም በአገሪቱ የሕግ የበላይነት እስኪሰፍን፣ ተጠያቂነት እስከሚረጋገጥ ድረስ የማያቆምና የሚቀጥል መሆን ይኖርበታል::** ቁጥራቸው የበዛ ሆኖም ስማቸው ይኽንን ያኽል ያልታወቀ ዜጎች እኮ በዚኽ አገዛዝ ከዓመት-ዓመት ሰብዓዊ መብታቸው ብቻ ሣይሆን ሰብዓዊ ክብራቸው እየተረገጠ ቀጥሏል:: የግፉ ምንጭ ካልደረቀ ደግሞ ወደ-ፊትም ይቀጥላል:: ምንጩ የሚደርቀው ደግሞ እነ አቶ መለስ ሥልጣን እንዲለቁ በማድረግ ብቻ አይወሰንም:: ኅብረተሰባችን ውስጥ ፍትኅን የሚያሰፍን ሥርዓት እንዲመጣ የሚያስችል ትግል በየራሣችንም ላይ፣ በየድርጅቶቻችንም ውስጥ ካልተደረገና አገር-አቀፍ፣ ማኅበረሰብ አቀፍ እንቅስቃሴ ለማድረግ ዝግጅቱ፣ ቁርጠኝነቱና ውሳኔው ከሌለን የመንግሥት ለውጥ እንኳን ቢደረግ የሕዝባችን መከራ ማክተሚያ አይኖረውም::

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ዓይነት በልዩ ልዩ ሰበብ በማንኛውም ዜጋ ላይ የሚደርስን ማናኛውንም የሰብዓዊ መብት ጥሰት በሃቅ የሚከታተልና ጎሣን፣ ቋንቋን፣ እምነትን፣ የፖለቲካ አቋምን፣ ወዘተ.. መሠረት ባደረገ ጠባብ አስተሣሰብ ሣይሆን በሰው ልጅ ሕይዎት ክቡርነትና እኩልነት፣ በፍትኅና ርትዕ መንፈስ በመቆም የሕግ ተገዥነትና የተጠያቂነት ባኅል እንዲኖር መታገል ያስፈልጋል:: ስለዚኽ ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ጊዜ በግፍ የታሠሩ እንዲፈቱ ስንጠይቅ ከዚኽ በአገራችን ላይና በኅብረተሰባችን ውስጥ ፍትኅ በዘለቄታዊነት እንዲሰፍን፣ የፖለቲካ እስር-ቤቶች እንዳይኖሩ ለማድረግ መሆን ይኖርበታል:: አለበለዚያ አገዛዙ በፈለገው ሰበብና ጊዜ የፈለገውን ሰው ያስራል፣ መሯሯጡ ሁሉና የትግል አጀንዳው የታሰሩትን በማስፈታቱ ላይ ይሆናል፣ ጫና ሲበዛ፣ አንዳንድ ጊዜም በጣም የከፋ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የተወሰኑትን ይፈታል፤ እንደገና

**ሁለት ፈትቶ አምሣ ያስራል፣ ወይም አሥር ገድሎ ሦስት ይፈታል፤ እንደዚኽ እያለ ሲፈልግ እያሰረ ሕዝቡን በማስቆጣት፣ እየፈታ ዝም በማሰኘት የትግል አጀንዳውን ለመቆጣጠር ከመሞከርና ሰብዓዊ መብትን ያኽል ከባድና መሠረታዊ ጉዳይን የፖለቲካ ጨዋታው መጠቀሚያ ማድረግና ለመሠረታዊ ለውጥ የሚደረገውን ትግል ለማዘናጋት ከመሞከር አይቆጠብም፡፡**

**ኢትዮጵያውያን በአገራችን ያሉ ችግሮች ተፈትተው ፍትኅን የሚያሰፍንና የሕግ የበላይነትንና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ሕዝባዊ (ዴሞክራሲያዊ) ሥርዓት እንዲመሠረት እንቅስቃሴአችን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን መሠረት ያደረገ ትግላችንም አገር-አቀፍ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ በተናጠል መታገል ተነጥሎ ከመመታት አያድንም፡፡ ልዩነት ላይ ቆሞና ኢትዮጵያውያንን እንደ አንዲት አገር ዜጎች የማያይ ትንሽ አስተሣሰብና እምነት ላይ ቆሞ  ሰብዓዊ ክብርን ማስከበር፣ መብቶችን ማረጋገጥ አጉል ምኞት ነው፡፡**

**እራሱ አገዛዙ ባዘጋጀውና ብዙ ቀዳዳዎችና ጉድለቶች በነበሩበት ምርጫ ሣይቀር ሕዝብ በቁርጠኝነት ተነሣስቶና በጎ ተስፋ ሰንቆ ድምፁን አመኔታውን ለጣለባቸው ሰጥቶ የመረጣቸውን ተወካዮችና እልፍ-አዕላፍ ደጋፊዎቻቸውን "የምን የሕዝብ ድምፅ፣ የበላይነት ያለውና ሚሰማው የኔ ድምፅ ብቻ ነው" ብሎ በዕብሪት እስር ቤት ማጎሩና ማሰቃየቱ አልበቃ ብሎ "መብታችን፣ ድምፃችን ይከበር" ብለው በሰላማዊ መንገድ ሕጋዊ ጥያቄ ስላቀረቡ ብቻ ለጨፈጨፋቸው ዜጎች "ተጠያቂ እኛ ነኝ፣ ሕገ-መንግሥቱን በጉልበት ለመናድ ተንቀሣቅሰናል፣.. ለዚኽም መንግሥትንም ሕዝብንም ይቅርታ እንጠይቃለን፣..." ብለው እንዲፈርሙ ያስገደደና ዓይኑን በጨው ታጥቦ "ጥፋተኞቹን በምኅረት ለቀናቸዋል" ብሎ የሚታበይ የነ አቶ መልስ አገዛዝ እነ ጋዜጠኛ እስክንድርን "አሸባሪ" ብሎ መወንጀሉ አዲስ ሆኖ ሊታይም ሆነ ሊያስገርም አይችልም፡፡ የሚያስገርመውና የሚያሣዝነው ይኸን አዲስ-ደራሽ አድርገን መቁጠራችን ብቻ ይመስለኛል፡፡**

**በአሁኑ ጊዜ በአንድ በኩል በግፍ የታሰሩ የኅሊና እስረኛ ወገኖቻችን በአስቸኳይ እንዲፈቱ፣ ታሳሪዎቹ በመረጧቸው የሕግ ባለሙያዎች አማካይነት ሕጋዊ ውክልና እንዲኖራቸው፣ በእስር ላይ እያሉም ሥነ-ልቦናዊና አካልዊ ጉዳት እንዳይደርስባቸው፣ የሐኪም እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው የሕክምና እርዳታ እንዲደረግላቸው፣ ቤተሰቦቻቸውና አገር-በቀልና ዓለም-አቀፍ ሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎችና ተቋማት በጠየቁ ጊዜ እንዲጎበኟቸው፤ ለቤተሰቦቻቸው መርጃም ይሁን ለጠበቆች ክፍያ መሸፈኛ የገንዘብ እርዳታ ማድረግ እንዲቻል አንድ ልዩ አለም-አቀፍ ግብረ-ኃይል ማቋቋሙ አስፈላጊ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በየጊዜው መርዶ ተቀባይነት የሚያስቀረው፣ በተናጠልና በየተራ ስቃይ መቀበልን ማስቆም የሚቻለውና ይኸንን ቀጣይ ግፍ ከምንጩ ለማድረቅ፣  በአገራችን ፍትኅን የሚያሰፍን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረቱ ስለ-ሆነ፣ ለዚኽ አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት እውን መሆን የሚደረገው ትግል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ላይ ተመሥርቶ በአገር-አቀፍ ደረጃ ሊደረግ ስለሚገባ በዚኽ ረገድ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በአፋጣኝ፣ ሆኖም በሰከነ መንገድ ማድረጉ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው እላለሁ፡፡**

**(*1)** ***ከዚኽ በላይ "በፈርስ የሚያጓጉር ከብት ብቻ ነው" የሚለው አባባል ቀደም-ሲል የኢዴኅ አባላት የነበሩትና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አገር-ወዳዶች ድርጅት በኋላም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር መሥራች፣ የትጥቅ ትግሉንም በምዕራብ ጎንደር በተለይ ላይና ታች አርማጩሆ ይመሩ የነበሩት ሻለቃ በሪሁን፣ ሻለቃ ዘለቀ ጀምበር እና ሻለቃ ደሴ አያልነህ ደርግ በእነሱ ላይ በተደጋጋሚ ያደረገውን ዘመቻ በተመለከተ ለድርጅታቸው (ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር) ከጻፉት ደብዳቤ ላይ የተወሰደ ነው፡፡ ደብዳቤው የደርግን ተደጋጋሚ ወታደራዊ ዘመቻዎች ለመቋቋም መድኃኒትን የመሣሰሉ አስፈላጊ እርዳታዎች እንዲደርሣቸው በዚያን ወቅት በድርጅቱ አመራርና በውጭ አገር (በሱዳን) ተወካዮች ሆነን ስንንቀሣቀስ ለነበርን ሰዎች ደጋግመው ለላኩዋቸው መልዕክቶች አጥጋቢ ምላሽ በወቅቱ ባለመድረሱ በመጨረሻ የጻፉልን ደብዳቤ ላይ ከብት ከአጠገቡ ያለው አምሣያው ተወስዶ ሲታረድ በዝምታ እንደሚያይና የታረደበት ቦታ ሲደርስ (ፈርስ ሲሸተው) ግን ድምፁን ከፍ አድርጎ እንደሚያሰማ (እንደሚያጓራ) የታወቀ ስለሆነ፣ እነሱም የጠየቁት እርዳታ በወቅቱ ካልደረሰና እራሣቸውን ለመከላከል ካልተጠቀሙበት እነሱ ከሞቱ በኋላ ቢደርስ እርባና የማይኖረውና የሚያፀፅት ከመሆን እንደማያልፍ ለማስገንዘብ የቀረበ አገላለጥ ነበር፡፡***

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**
**ድል በአምባ-ገነንና በግፈኛ ሥርዓቶች ላይ!**